**የበልግ 2021 የድንበር ሂደት ፡- የድኅረ ማጽደቅ ማሳወቂያ ደብዳቤ በገንስተን መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለ6-7 ክፍል ተማሪዎች ቤተሰቦች**

ዲሴምብር 10፣ 2021

ውድ የገንስተን ቤተሰቦች ፡-

የትምህርት ቤቱ ቦርድ በዲሴምበር 2 ቀን 2021 ባካሄደው ስብሰባ ከኦገስት 2022 ጀምሮ ተፈጻሚነት የሚኖረውን የበልግ 2021 የድንበር ማሻሻያ በማጽደቅ ድምጽ ሰጥቷል፡፡

የ46140፣ 48150፣ 48280፣ 48281 እና 48290 የዕቅድ ዩኒቶች ከ2022-23 የትምህርት ዘመን ጀምሮ ከገንስተን ወደ ጄፈርሰን መካከለኛ ትምህርት ቤት ተመድበዋል፡፡ ይህ ለውጥ ለሁሉም አዲስ ገቢ 6ኛ ክፍል ተማሪዎች (በ2021-22 የ5ኛ ክፍል ተማሪዎች) እንዲሁም ከላይ በተዘረዘሩት የዕቅድ ዩኒቶች ውስጥ ነዋሪ ለሆኑ የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ በገንስተን የሚማሩ ወይም ከጁን 17 2021 በፊት በገንስተን የሚገቡ የ6ኛ ወይም 7ኛ ክፍል ተማሪዎች የ8ኛ ክፍል ትምህርታቸውን እስኪያጠናቅቁ ድረስ በገንስተን መቀጠል ወይም በ2022-23 አዲስ በተመደቡበት የአካባቢው ትምህርት ቤት (ጄፈርሰን መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት) መቀጠል ይችላሉ፡፡ በገንስተን ለመቀጠል የሚፈልጉ ተማሪዎች ማድረግ የሚጠበቅባቸው ነገር የለም፡፡ **አሁን 6ኛ -7ኛ ክፍል ያሉ ልጆቻቸው ትምህርት ቤት ቀይረው ከ2022-23 የትምህርት ዘመን ጀምሮ በጄፈርሰን መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንዲማሩ የሚፈልጉ ቤተሰቦች እስከ ጃንዋሪ 27 ቀን 2022 ከዚህ የሚከተሉትን እርምጃዎች መውሰድ አለባቸው ፡-**

- በ2022-23 የትምህርት ዘመን ልጅዎ በጄፈርሰን መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንደሚማመር/ እንደምትማር ለማሳወቅ እባክዎን ለገንስተን ሬጅስትራር ያሳውቁ፡፡
- ሚስስ ቪላሮኤል በኢሜል villaroel@apsva.us ወይም በስልክ ቁጥር 703-228-6909 ይገኛሉ፡፡

***ወንድምና እህቶች፣ እና የትራንስፖርት መረጃ***

- ***ወንድሞችና እህቶች፡-*** በገንስተን የ6ኛ -7ኛ ክፍል ተማሪዎች ወንድሞች/ እህቶች የሆኑ የ5ኛ ክፍል ተማሪዎች ከተመደቡት የዕቅድ ዩኒቶች ውስጥ በአንዱ ነዋሪ የሆኑ  በ2022-23 የትምህርት ዘመን ወደ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲገቡ ከታላላቅ ከወንድሞቻቸው ወይም እህቶቻቸው ጋር በገንስተን አብረው መማር እንዲችሉ ሊዘዋወሩ ይችላሉ፡፡

- ***ትራንስፖርት ፡-*** የአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ከላይ በሚገኙት የዕቅድ ዩኒቶች ውስጥ ያሉ ነገር ግን በእግር ከሚደረስበት ዞን ውጪ ነዋሪ ለሆኑ ተማሪዎች በገንስተን ቢቀጥሉም ሆነ በጄፈርሰን ትምህርት ቤት ለመማር ቢመርጡ (በቅርቡ የተመደበ የአካባቢ ትምህርት ቤት) ትራንስፖርት ያቀርባል፡፡ በእነዚህ የዕቅድ ዩኒቶች ውስጥ በአሁኑ ጊዜ  ከ6ኛ-7ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች በገንስተን ከቀጠሉ በሀብ ስቶፕስ አማካኝነት የትራንስፖርት አገልግሎት ያገኛሉ፡፡

ማንኛውም ጥያቄ ካለዎት፣ ተመራጩ ጥያቄዎን የማቅረብ ዘዴ በengage@apsva.us ኢሜል ማድረግ ወይም በስልክ ቁጥር 703-228-2481 የዕቅድ እና ግምገማ ክፍልን ማነጋገር ነው፡፡ የበልግ 2021 የድንበር ሂደትን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ከዚህ የሚከተለውን ሊንክ ይጎብኙ፡- https://www.apsva.us/engage/fall-2021-boundary-process፡፡

አመሰግናለሁ፣

ሊሳ ስቴንግል
የዕቅድ እና ግምገማ ዳይሬክተር
አርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች